እትም ቁ.12 እ.ኤ.አ.ሚያዚያ 30, 2016

# ዜና ውሃ ራስ አገዝ  አቅርቦት

ዜና ሰልፍ ሰፕላይ በየሁለት ወሩ አንዴ በ ሰልፍ ሰፕላይ ግብረ ሐይል በኢትዩጵያ አማካይነት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ግብረ ሐይል በመንግስት ተቋማትና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ሮረም ነው፡፡ የጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ዜና በማዘጋጀት ረገድ ቅድሚያውን ወስዷል፡፡

## የራስ አገዝ የውሃ  ተቋማት ኤግዚብሽንና ባዛር!
## ቁልፍ የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ተዋናዮች የተገናኙበት መድረክ



የተለያዩ ተዋንያኖች በኤግዚብሽኑ ላይ ተከፍለዋል (የኤግዚብሽኑ ገፅታ በከፊል)

ከባለፈው አመት ልምድ በመነሳት ብሔራዊው የራስ አገዝ / Self Supply/ ግብረ ሀይል የውሃ ቀንን ምክንያት በማድረግ ለሶስት ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ.ከመጋቢት 18 እስከ 21 2018ዓ.ም አዘጋጅቶ ነበር፡፡

የኤግዚብሽኑም ዋና ዓላማ እርስ በእርስ ለመማማር የልምድ ልውውጥ ማድረግ ሲሆን የተገኙ እድሎችን ከባለድርሻ አካላት (ማለትም ከፓሊሲ አውጪዎች ከግል ሴክተር ከመንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ግብረሰናይ ድርጅቶች እና ከሴክተሩ ፈፃሚዎች ጋር በአባወራ ደረጃ እየተከናወነ ስላለው ኢንቨስትመንትዎች እና የተደረጉ ስላሉ ቅስቀሳዎች ውይይትና ምክክር ተደርጓል፡፡



ክቡር አቶ ጀምስ ዴንግቾልቶት በዋና መ/ቤት ቅጥር ጊቢ ኤግዚብሽኑንና ባዛሩን ሲከፍቱ

(ፎቶ በዋስ ሮፐስ)

ለኤግዚቢሽኑ ላይ የተለያዩ ምርቶችና አገልግሎት ሰጪዎች በራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ዙሪያ በተያያዘ በሚኒስትር መስሪያ ቤት ጊቢ ውስጥ ቀርቧል፡፡ በዚህም ኤግዚብሽን ከ40 በላይ የኤግዚቢሽን ተካፋዮች የተለያዩ የቤት ውስጥ ውሃ መሳቢያ ምርቶችን ማንዋል ሊንግ መሳሪያዎች የተለያዩ በሜካኒካዊ መንገድ የሚሰሩ የውሃ ፓምፖች እና የተለያዩ የውሃ ፓምፕ ፒቪሲ ቱቦዎች አቅራቢዎች ቀርቧል፡፡በተጨማሪም በደብብ ክልል በስፋት በራስ አገዝ ውሃ ተቋማት ግንባታ ዙሪያ ትልቁን ሚና እየተጫወተ ያለው የደቡብ ክልል ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ እየሰጠ ያለውን የብድር አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉ ዕድሎችን በስፋት ለታዳሚዎቹ አቅርቧል፡፡

### ልዩ ዕትም የሰልፍ ሰፕላይ ኤግዚብሽንና ባዛር

- ለቁልፍ ሰልፍ ሰፕላይ አክሰሌሬሽን ተዋንያኖች የመገናኘት የተፈጠረ ዕድል
- ሰልፍ ሰፕላይ ሴሚናር የኔ ውሃ ፣ የኔ ስራ ሐገራዊ የስራ ተነሳሽነትን ማበረታታት በተጨማሪም የዩኒቨርሳል አክሰስ ደህንነቱ የተጠበቀ የውሃ አቅራቦት
- የባለገመድ ፓምፕ ቻምዮን ሽልማት
- የሰልፍ ሰፕላይ ቢዚነስ ካታሎግ እ.ኤ.አ 2016 ተዘጋጅቷል
- ሰልፍ ሰፕላይን ለማስፋፋት የተለያዩ ኢቨንቶች ጎን ለጎን ተደርጓል

### ማውጫ

ከአቻ አካላት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች
- ማስታወቂያ የዋሽ ቢዚነስ ሐሳቡዎን  አዲሱን ቻሌንጅ ፈንድ በማሸነፉ ያስፉ
- መረጃ
- የተሰሩ ስራዎች እና በመጪው ጊዜ የሚሰሩ ስራዎች













ከ 40 በላይ ድርጅቶች የተሳተፉበት የዚህ ዓመት ኤግዚብሽን ሁሉም ድርጅቶች የራሳቸው ምርትና አገልግሎታቸውን አቅርበዋል፡፡በአጋጣሚውም ለተለያዩ ድርጅቶች ዕውቀት የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ተጠቅመውበታል፡፡

## ሰልፍ ሰፕላይ ሴሚናር
## የኔ ውሃ ፤ የኔ ስራ ሐገራዊ ተነሳሺነት እና ትውውቅ

በሌላ መልኩ ደግሞ ይህንኑ ኤግዚብሽንና ባዛር ተንተርሶ የአንድ ቀን ሴሚናር መጋቢት 15፡ 2008ዓ.ም በጌት ፋም ሆቴል የቀረበ ሲሆን በስብሰባው ላይ 135 ያህል ተሳታፊዎች ከተለያዩ አካላት ማለትም ከመንግስት ከግብረሰናይ ድርጅቶች ከግል ሴክተርና ከተጠቃሚዎች የተውጣጡ ናቸው፡፡ሴሚናሩን በንግግር የከፈቱት አቶ ታመነ ሀይሉ የገጠርና የብሔራዊ ዋሽ አቀናጅ ሲሆኑ በጃይካ ኢትዮጵያ ቢሮ አቶ ታካሐሽ ማቱኢሲያማ /Takashi Matsuyama ሴሚናሩ መከፈቱን በጋራ አብስረዋል፡፡



በጌት ፋም ሆቴል አዲስ አበባ በተደረገው ኮንፍረንስ ከ130 በላይ ሰዎች ተሰብስበው ነበር::



አቶ ታመነ ሐይሉ የገጠር ዋሽ እና በሚኒስትር መ/ቤት አስተባባሪ (በስተቀኝ)እና አቶ ማቱኩያማ(ባራ) በሴሚናሩ ላይ በመገኘት ንግግር አድርገው ነበር

ወደ 10 የሚጠጉ ጹሁፎች በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የቀረበ ሲሆን እየተከናወኑ ስላሉ እንቅስቃሴዎች ሰፋ ያለ ምክክር ተደርጓል፡፡በተለይም በራስ አገዝ የቦዮ ጋዝ አጠቃቀም አቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ከራስ አገዝ አቀጣጣዮች ጋር ያለውን ተያያዥነትና ከማይክሮ ተቋማት ጋር ስለብድር አቅርቦት ዙሪያ በሰፊው ዳሰሳ የተደረገበት ርዕስ ናቸው፡፡

### From Implementing Partners

- “Local people do not stop if they know the benefit” - Interview of Mr.Atnafu Asfaw, Deputy Head of TVET

# የገመድ ፓምፕ ሻፒዎን ተሸላሚዎች

የተለያዩ የራስ አገዝ ተዋንያኖች በጃይካ ዋስ ሮፕስ የተለያዩ ሽልማቶች ተሰጣቸው፡፡እነዚህ የተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት ከአምራቾች፣ ከተካዮች ከወረዳ ቢሮዎች ከተጠቃሚዎች እና ከአከባቢ ባለሙያተኞች የተውጣጣ ነበር፡፡

ለተሸላሚዎች የተለያዩ ዕቃዎችና ሰርተፍኬቶች በሽልማት መልክ የተበረከቱ ሲሆን ሽልማቱንም ከውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር በመጡ ተሳታፊዎች እና በተለያዩ አካላት ተበርክቷል፡፡የተለያዩ የግድግዳ ሰዓቶች የውሃ ማጣሪያ መቆሚዎች እና የውሃ ማጣሪያ ዕቃዎች ለተሸላሚዎች ተሰጥቷል፡፡





## መሪ የባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭት ተዋናዮችና ተሸላሚዎች

| የአሸናፊው ስም | የሽልማቱ ምድብ | የድርጅቱ ስም |
|---|---|---|
| የብድን ሽልማት | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ ብድር ተቋም | የይርጋጨፌ ወረዳ ኦሞ - ማይክሮ ፋይናንስ |
| አቶ መሀመድ ሻፎ | መሪ የአከባቢ ባለሙያ | የአከባቢ ባለሙያ መስቀን ወረዳ |
| አቶ ወንድሙ ላንቃሞ | መሪ የአከባቢ ባለሙያ እና የምርጥ ስራ ባለቤት | የአከባቢ ባለሙያ ዳሌ ወረዳ |
| አቶ በየነ ዱካሞ | ምርጥ የአከባቢ ባለሙያና ንቁ ተሳትፎ | የአከባቢ ባለሙያ ዳሌ ወረዳ |
| አቶ ጌታቸው መሀመድ | ምርጥ የባለሙያ ፓምፕ አምራች | አምራች ከጃይካ |
| አቶ ጢሞቲዎስ መሀሪ | ምርጥ የባለገመድ ፓምፕ ሻጪ | አምራች ከወላይታ ሶዶ |
| አቶ አትክልት ግርማይ | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች | አምራች ከአዲስ አበባ |
| አቶ ታረቀኝ ሐይሌ | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ አሰልጣኝ | አስልጣኝ -ከወላይታ ሶዶ ቴክኒካ እና ሙያ |
| አቶ ታደሰ በዴቾ | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ ጠጋኝና ተጠቃሚ | የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ ይርጋጨፌ |
| አቶ በላይ በልጉዳ | የመጀመሪያው የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ | የባለ ገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ ከዳሌ |
| የቡድን ሽልማት | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ አስተላላፊ | የወልቂጤ ቴክኒክ እና ሙያ ተቋም |
| የቡድን ሽልማት | ምርጥ የባለ ገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ አስተላላፊ | የአርባ ምንጭ ቴክኒክ እና ሙያ ተቋም |
| የቡድን ሽልማት | በባለ ገመድ ፓምፕ መልካም ስራ | የዳሌ ወረዳ ውሃ ቢሮ |
| የብድን ሽልማት | በባለ ገመድ ፓምፕ መልካም ስራ | የዳሞት ፐላሳ ወረዳ ውሃ ቢሮ |
| የቡድን ሽልማት | በባለ ገመድ ፓምፕ መልካም ስራ | የመስቀን ወረዳ ውሃ ቢሮ |
| የቡድን ሽልማት | በባለ ገመድ ፓምፕ ምልካም ስራ | የይርጋጨፌ ወረዳ ውሃ ቢሮ |

# የሰልፍ ሰፕላይ የቢዚነስ ካታሎግ ተዘጋጀ

"የኔ ውሃ የኔ ስራ ነው" በሚል ርዕስ የራስ አገዝ ትርኢትና ሲሚናር በአዲስ አበባ እ.ኤ.አ ከመጋቢት 21 እስከ 23 2016 ተካሆደ፡፡ከ40 በላይ የሆኑ ኢግዚቢተሮች አገልግሎታቸውንና ምርቶቻቸውን ሸጠዋል፣ አስተዋውቀዋልም፡፡ከዝግጅቶችም መካከል ሁለተኛው የራስ አገዝ ቢዝነስ ካታሎግ ትኩረቱን በራስ አገዝ ላይ ያደረገ ዕትም ለተሳታፊዎች ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ የቢዚነስ ካታሎግ የተለያዩ የቢዚነስ ፈጣሪዎች/ኢንተርፕነሮች/ እና በዋሽ ሴክተር የሚገኙ የራስ አገዝ አቀጣጣዮች ተካተውበታል፡፡እነዚህ የተለያዩ የቢዚነስ አካላት ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን የሸጡና ያስተዋወቁ ሲሆን በዚህም የንፅህ ውሃ አቅርቦትን እና ንፅህናን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሻሽል ይጠብቃል፡፡


የቢዚነስ አካላት ምርቶቻቸውን ማስፋፋትና ተቀናጅተው መስራት እንደሚፈልጉ አስታውቀዋል፡፡የሁለተኛው የቢዚነስ ካታሎግ በፊት ከነበረው ተሻሽሎ የቀረበና አዳዲስ አቅራቢዎችም የተካተቱበት ካታሎግ ስለ እያንዳንዱ ድርጅት በቂ መረጃ የሚሰጥ የአምራቾችን አድራሻን ያካተተ እንደማጣቃሻ ሰነድ ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡


አብዛኞቹ አምራቾች በትርዒቱ ላይ ተሳትፎ ያደርጉ ሲሆን ከሌላ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ፍቃደኛ ናቸው፡፡እያንዳንዱ የቢዚነስ ቡድን ስለ ምርቶቻቸው በቂ መረጃ ያስቀመጡ ሲሆን ምን እንደሚፈለጉም በግልፅ ፍላጎታቸውን አንፀባርቀዋል፡፡ ይህን ካታሎግ ለማየትና ምርቶቻቸውን ለመጠቀም ጥቂትም ቢሆን በኢትዮጲያ እየተካሄደ ላለው የራስ አገዝ ንቅናቄ አስተዋፆ ያደረጉ እነዚህ አምራቾች በመንብኘት ስራ ይፍጠሩያሎትን ማንኛውንም አስተያየት ጥያቄ እና ሐሳብ ካሎት የሚከተሉትን አድራሻ ይጠቀሙ፡፡

አብዛኞቹ የኤግዚብሽኑ ተካፋዮች እ.ኤ.አ 2015/16 በተካሄደው የሰልፍ ሰፕላይ ኤግዚብሽንና ባዛር ላይ ተሳታፊ የነበሩና በዚያኑ አመት ላይ በወጣው ቢዚነስ ካታሎግ ላይ የወጡ ናቸው በዚህ ዕትም ደግሞ ስራቸው እና መሰረታዊ መረጃን ጨምሮ አድራሻቸውም ተካቷል፡፡

አቅራቢዎች የአነስተኛ ቴክኖሎጂ ዕቃ አምራቾች በካታሎግ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል (ከላይ) በተጨማሪም የሰለጠኑ የአከባቢ ባለሙያዎች በተከላ አሰራርና ጥገና በአባቢ ባለሙያዎች ካታሎግ ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል (ከታች)

Email:- b.demke@quaforall.org




አብዛኞቹ የኤግዚብሽኑ ተካፋዮች እ.ኤ.አ 2015/16 በተካሄደው የሰልፍ ሰፕላይ ኤግዚብሽንና ባዛር ላይ ተሳታፊ የነበሩና በዛኑ አመት ላይ ለወጣው ቢዚነስ ካታሎግ ላይ የወጡ ናቸው በዚህ ዕትም ደግሞ ስራቸው እና መሰረታዊ መረጃን ጨምሮ አድራሻቸውንም ተካቷል፡፡
አቅራቢዎች የአነስተኛ ቴክኖሎጂ ዕቃ አምራቾች በካታሎግ ለማስተዋወቅ ተሞክሯል (ከላይ) በተጨማሪም የሰለጠኑ የአከባቢ ባለሙያዎች በተከላ አሰራርና ጥገና በአባቢ ባለሙያዎች ካታሎግ ውስጥ ለማካተት ተሞክሯል (ከታች)

**As an output of the fair, business enterprise catalog, and blogs were produced and can be accessed at the following:**

# የራስ አገዝ የውሃ ተቋማት ዋና ዋና ተዋናዮች በባለ ገመድ ፓምፕ ዙሪያ ውይይት አደረጉ

የውሃ ቀንን ተተርሶ በተካሄደው የሶስት ቀናት ኤግዚቢሽንና ሴሚናር በጃይካ ዋስ ሮፕስ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዚህ የራስ አገዝ የባለ ድርሻ አካላት ኮንፍረንስ፣ በባለ ገመድ ፓምፕ ጥራት ቁጥጥር ዙሪያ እና እየተደረጉ ስላሉ እንቅስቃሴዎች ውይይት እና ገለፃ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የቢዚነስ ፈጠራ ወርክ ሾፕ የተደረገ ሲሆን እንዴት የራስ የቢዝነስ ፈጠራ ባለ ራዕይ መሆን እንደሚችል ከግል አገልግሎት ሰጪ ከተወጣጡ አካላት ውይይት ተደርጓል፡፡በውይይቱም ፈጠራን እንዴት ምርትን ማስተዋወቅ እንደሚቻል እና የደንበኛ አያያዝ ጨምሮ በቂ ውይይቶች ተደርጓል፡፡ በተያያዘ ዜና በብድር አመላለስ ዙሪያ የገጠሙ ችግሮች እና መፍቴዎቻቸው ጨምሮ በተሳታፊዎች እና በተጠቃሚዎች ተመክሮበታል፡፡



አቶ ታመነ ሐይሌ የገጠር ዋሽና በሚኒስትር መ/ቤት አስተባበር በሴሚናሩ ላይ በመገኘት ለባለገመድ ፓምፕ ባለድርሻ አካላት የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ



የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲዩት የአከባቢ ባለሙያዎች እና የወረዳ የመንግስት አካላት በብድር አከፋፈል ዙሪያ ያደረጉት ውይይት በከፋል (እ.ኤ.አ መጋቢት 21 2016)



የቢዚነስ ስኪል ስልጠና እንዴት ለባለገመድ ፓምፕ ስርጭት የገበያ እንቅስቃሴ ዙሪያ ውይይት ተደርጓል፡፡ ተሳታፊዎች በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ የተነሱት ፎቶ /እ.ኤ.አ መጋቢት 22 2016/





የተለያዩ ዶክመንቶች ቡክሌቶች ዕቃዎች ከባለገመድ ፓምፕ ስርጭትና ትውውቅ ተሳታፊዎች ተሰራጭቶ ነበር፡፡

## የዋሽ የቢዚነስዎን ሐሳብዎን ያሳድጉ
## አይ አር ሲ ከምንሊንየም ውሃ አሊያንስ ጋር ለመጣመር ቻሌጅ ፈንድ አዘጋጅቷል በፈንዱም 75000 ብር የሚጠጋ ለአሸናፊዎች ተዘጋጅቷል

**Aqua for All**

### ቻሌንጅ ፈንድ ለምን ?

የግሉን ሴክተር ተሳትፎ በዘላቂ ንፁህ ውሀ አቅርቦትና የውሃ ንፅህና አሰጣጥ በቤትለቤት ተሳትፎ ለማነቃቃትና በምርቶችና አገልግሎቶቻቸው ዙሪያ ድጋፍ ለማድረግ ሲባል ይህን ቻሌንጅ ፈንድ አዘጋጅቷል፡ይህ ቻሌንጅ ፈንድ ድጋፍ ለማድረግ የሚፈልገው በግሉ ዙሪያ ማለትም ለአከባቢ ባለሙያዎች፣ ለአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢነተርፕራይዞች፣ ለአምራቾች ፣ ለአከፋፋዮች ሆኖ የሚሰጡት አገልግሎት ሆነ ምርት ከውሃ እና ከውሃ ንፅህና የተያያዘ ሆኖ የስራው ስፋት በማሕበረሰብ ደረጃ በወረዳ አሊያም በቀበሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ለበለጠ መረጃ ይህን ድህረ ገፅ ይጠቀሙ B.Damte@aquaforall.org / Or Call +251-911 76 97 90

## የራስ አገዝ የማፋጠን እንቅስቃሴዎችን ያካፍሉ

የራስ አገዝ ዜና በሁለት ወር አንዴ በራስ አገዝ ግብረ ሐይል በኢትዮጵያ አማካይነት ይታተማል፡፡ ግብረሀይሉም ከመንግስት ተቋማት እና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ፎረም ነው፡፡ ዜና ራስ አገዝ ተመዝግበው ለሚከፍሉ አካላቶች በኢ-ሜይል የሚላክ ሲሆን በተጨማሪም ዜናውን በአይ አር ሲ ድህረ ገፅ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ዌብ ሳይቱ ከሌሎች አለም አቀፍ ሳይቶች ጋር በማስተዋወቅ የኔትወርክ ትስስርን ይፈጥራል፡፡በዚህ ራስ አገዝ ዜና ላይ የገጠመዎትን ችግር ያስመዘገቡት ዕመረታ እና እንዲታወቁለት የሚፈልጉትን እንቅስቃሴዎን ይንገሩን ያካፍሉን፡፡ ለዚህም እንዲረዳዎት ለጃይካ ዋስ ሮፐስ አጋር ድርጅት ያነጋግሩ አሊያም በአድራሻው ይላኩ፡፡

---

### እ.ኤ.አ በየካቲት በመጋቢትና በሚያዝያ የሚከናወኑ ክንውኖች

| | |
|---|---|
| የካቲት 10-11 | የውሀ ጉድጓድ ሽፋንና የግድጓ አፍ ማጥበቢያ የመስራት ስልጠና |
| መጋቢት 4-5 | የባለ ገመድ ፓምፕ አምራቾች እና ተካዮች የሰርተፍኬት ሂደት/ጃይካ ዋስ- ሮፐስ/ |
| መጋቢት 7-12 | የአከባቢ ባለሙያዎች የማነቃቂያ ስልጠና በመስቃን /ጃይካ ዋስ - ሮፐስ/ |
| መጋቢት 20-22 | የባለ ገመድ ፓምፕ የባለድርሻ አካላት ስብሰባ ለባለገመድ ፓምፕ የተዘጋጀ የብድር ሲስተም እና የአመላለስ ስብሰባ የቢዚነስ ስሲል ስልጠና /ጃይካ ዋስ- ሮፐስ/ |
| መጋቢት 21-23 | የአለም ውሃ ቀን አከባቢ እና የራስ አገዝ ትርኢት /በራስ አገዝ ግብረ ሀይል/ |
| - | የማህበረሰብ ስብሰባ የባለ ገመድ ፓምፕን የማስተዋወቅና የመትከል በአከባቢ ባለሙያዎች ከቢዚነስ አንፃር |
| - | በአባወራ ደረጃ ፍላጎት መፍጠርና የራስ አጋዝ አተገባበር በራስ አገዝ አክሰለሬሽን ፕሮጀክት ወረዳዎች |
| - | ቲዎቲ ርቪው /ጃይካ ዋስ ሮፐስ/ |
| ሚያዝያ 4-9 | የባለ ገመድ ፓምፕ የውስጥ ጥራት ቼክ ሊስት ለአምራቾች /ጃይካ ዋስ ሮፐስ/ |

### እ. ኤ. አ በሚያዝያ እና ግንቦት 2016 የድርጊት መርሐ - ግብር

- ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ የማነጂመንት ቡድን ስብሰባ የሰልፍ ሰፕላይ አክሰሌሬሽን የአጋሮች ክንውን
- በአባ ወራ ደረጃ ፋላጎት በሰልፍ ሰፕላ ዙሪያ ከአጋሮች ጋር ለመሆን በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ ሰልፍ ሰፕላይ አክሰለሬሽን በሚሰራቸው ወረዳዎች
- ማሕበረሰብ አቀፍ የባለገመድ ፓምፕ የማስተዋወቅ እና የተከላ ከስራ ፈጠራ ጋር ተያይዞ ለአባቢ ባለሙያዎች (ዋስ- ሮፐስ ፕሮጀክት)
- የውሀ ጉድጓድ ሽፋንየማምረት ስልጠና በይርጋጨፌ (በዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት)
- የባለገመድ ፓምፕ ተከላ ስልጠና በደቡብ ክልል የ10000 ባለገመድ ፓምፕ ስርጭት (በዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት)
- የባለገመድ ፓምፕ የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ስልጠና ለ አምራቾች (ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት)

If you have any comments, questions,
suggestions, please contact us at;
**JICA WAS-RoPSS Project**
Room # 012, Ministry of Water, Irrigation and Electricity
Tel: +251 - (0)11-651-1455
Mob: +251 - (0)935-353210/12/14
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com
http://www.jica.go.jp/oda/project/1100485/index.html (jp)
http://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/004/index.html (en)

Websites

| | |
|---|---|
| MoWIE | http://www.mowr.gov.et/ |
| CoWASH | http://www.cmpethiopia.org/ |
| IRC | http://www.ircwash.org/ |
| A4A | http://www.aquaforall.org/ |
| Water.Org | http://water.org/ |
| RWSN | http://www.rural-water-supply.net/en/resources/details/662 |